# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 240 ታህሳስ ፲፩ 2005 ገጽ 1

አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ሁለገብ ትግልን እንደ አማራጭ ሲያቀርብ የሰላማዊ ትግልን ውበት በመጠራጠር አልነበረም። ሰላምን መመኘት፣ ስለሰላም መዘመር፣ ስለሰላም ማስተማር፣ ስለሰላም መስበክ በእርግጥ ሰላምን ያስገኛል? ሰላም የሚደፈርሰው ሰዎች ስለሰላም ጥሩነት በቂ ግንዛቤ ስለሌላቸው ነውን? በጭራሽ! ሰላምን መመኘት፣ ስለሰላም መዘመር፣ ማስተማርና መስበክ ጥቅም ቢኖራቸውም ሰላምን ለማስገኘት በቂ አይደሉም፤ ሆነውም አያውቁም። ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የግንቦት 7 ሕዝባዊ ኃይል ተመሰረተ

www.ginbot7pf.org በሚል ድረ ገጽ ላይ የወጣው መግለጫ እንደሚያመለክተው የግንቦት 7 ህዝባዊ ሃይል የሚባል ድርጅት መመስረቱ ተገለጸ ። መግለጫውን ያወጣው የግንቦት ሰባት ህዝባዊ ሃይል እንዳብራራው ታህሳስ ፲፩ ቀን 2012 ዓም " የወያኔን ዘረኛና አምባገነን አገዛዝ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ በትጥቅ ትግል ለማስወገድ "የግንቦት7 ሕዝባዊ ኃይል" የሚል ስያሜ የሰጠነውን፣ በሃገር ወዳድና ለህዝብ ተቆርቋሪ በሆኑ ወጣቶች፣ ምሁራንና ዜጎች የተሞላውን ድርጅት መመሥረታችን በዛሬው እለት ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በይፋ እናበስራልን" ብሎአል።

"የሕዝብ ሉዓላዊ የሥልጣን ባለቤትነት የተረጋገጠባት፤ የዜጎች መብቶች፣ ሃገራዊ አንድነት፣ ደህንነትና ጥቅም የተከበሩባት ጠንካራና ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ እውን ሆኖ የማየትን ራዕይ የሰነቀ ድርጅት መሆኑን" የገለጸው ህዝባዊ ሀይሉ፣ መንግስትን በኃይል የማስወገድ፤ ሰላማዊና ዲሞክራሲ የሥልጣን ሽግግር በሃገሪቱ እንዲኖር የማስቻል እና ከማንኛዉም የፓለቲካ ድርጅት ጋር ያልወገኑ ነፃ፣ ጠንካራና ብቃት ያላቸው ህገ-መንግሥታዊ የመከላከያ፣ የፖሊስና የደህንነት ተቋማት እንዲኖሩ አስተዋጽዖ የማድረግ ተልዕኮ" ይዞ መነሳቱን ገልጿል።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በሃይማኖት ላይ የሚያደርገውን ጣልቃ ገብነት አጠናክሮ ቀጥሏል። ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አሁንም የወያኔ ቀኝ እጂ ፓትሪያርክ እየተፈለገ ነው

ሁሉ ነገር ውስጥ ጣልቃ ካልገባ ሞቶ የሚያድር የሚመስለው የወያኔ ዘረኛ አገዛዝ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባቱን በማጠናከር አዲስ ፓትርያርክ ለማስመረጥ አስመራጭ ኮሚቴ እንዲቋቋም ማድረጉን ከአዲስ አበባ ዘጋቢያችን በላከልን ሪፖርት ገለጸ። እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት የተወሰኑ ጳጳሳት ድርጊቱን በግልጽና በጽኑ የተቃወሙ ሲሆን በአስመራጭ ኮሚቴነት የተሰየሙት አባላት አብዛኞቹ የሚቹ አቡነ ጳውሎስ ቀን እጂ የነበሩ ሆድ አደሮች መሆናቸው ታውቋል።

ዘጋቢያችን እንዳለው ይህን የማናለብኝ ድርጊት ከተቃወሙት መካከል አቡነ ገሪማ፣አቡነ አትናቲዎስ፣አቡነ ቄርሎስ፣አቡነ ቀውስጦስና አቡነ ሉቃስ ይገኙበታል። በተለይም በቅርቡ በዩናይትድ ስቴትስ ተደርጎ በነበረው የእርቀ ሰላም ጉባኤ ላይ ተሳትፈው የተመለሱት አባቶች አስመራጭ ኮሚቴ ባቋቋመው በዚህ የሲኖዶስ ስብሰባ ላይ አልተሳተፉም።ቀሪዎቹም ረግጠው በመውጣትና በዝምታ ተቃውሟቸውን መግለጻቸውም ታውቋል።

ተቃውሟቸውን ከገለጹት አባቶች መካከል የዘጋቢያችን ምንጭ ያነጋገራቸው አንድ አባት በሁለቱ ሲኖዶሶች መካከል የተጀመረው የእርቀ ሰላም ውይይት አንዳች እልባት ሳያገኝ ወኪል ለማስቀመጥ በወያኔ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## አራት ኢትዮጵያዊያን ጋዜጠኞች በነጻነት የሔልማን ሃሜት የመናገር ሽልማት አሸናፊዎች ሆኑ

ከኒውዮርክ ይወታ ዘገባ እንደሚያመለክተው አራት ኢትዮጵያዊያን ጋዜጠኞች የ2012 ን በነጻነት የመናገር ሽልማት አሸናፊ መሆናቸው የታወቀ ሲሆን ይህን ሽልማትም ያገኑት በዓለማችን የመናገር ነጻነት ተረግጦና ታፍኖ በሚገኝባት ኢትዮጵያ በነጻነት ሃሳብን የመግለጽ መብት ለመጠቀም ያደረጉትን ጽናትና ርምጃ ከግምንት ውስጥ በማስገባት መሆኑን ዘገባው አመልክቷል። ተሸላሚዎቹ ታዋቂዎቹና በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የጭካኔ ርምጃ በእስር ላይ የሚገኙት ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋና ርእዮት ዓለሙ፣ እንዲሁም የአውራምባ ታይምሱ ጋዜጠኛ ውብሸት ታየና እንዲሁም የአዲስ ነገር ኦን ላይኑ መስፍን ነጋሽ መሆናቸው ታውቋል። እነኝህ አራት ኢትዮጵያዊያን ጋዜጠኞች ለዚህ ዓለም አቀፍ ሽልማት የበቁት ከ 19 ሃገራት መካከል ከ41 ጋዜጠኞች ጋር ተወዳድረው ባገኙት ብልጫ መሆኑ ታውቋል።

አራቱም ተሸላሚ ጋዜተኞች በግፈኛአው የወያኔ አገዛዝ አሻንጉሊት ፍርድ ቤት ሽብርተኞች ናችሁ ተብለው የተከሰሱ መሆኑ በስፋት ሲዘገብ (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## መስፍን ኢንጂነሪንግ ኩባንያ የ2.6 ቢሊዮን ብር ኮንትራት ተሰጠው

ባለቤትነቱ የሕወሀት የሆነው መስፍን ኢንጂነሪንግ ኩባንያ ከሶስት የስኳር ፋብሪካዎች የ2.6 ቢሊዮን ብር ኮንትራት እንደወሰደ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ዘገበ። ከተቋቋመ 19 አመት የሞላውና የትግራይ መልሶ ማቋቋም ኢንዳውመንት ፈንድ የተሰኘው ግዙፍ ድርጅት አካል የሆነው መስፍን ኢንጂነሪንግ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገነቡ 3 ስኳር ፋብሪካዎች የሚሆኑ የማፍሊያ ቤቶችን (ቦይሊንግ ሀውሶች) ለመገንባት ነው የ2.6 ቢሊዮን ብሩን ኮንትራት የወሰደው። የመስፍን ኢንጂነሪንግ ምክትል ስራ አስኪያጅ አቶ አማኑኤል ገብረኪዳን ለኢቲቪ እንደገለጹት፤ ፋብሪካው ከ2 ዓመት በሁዋላ አመታዊ ትርፉን ወደ 600 ሚሊዮን ብር ለማሳደግ እየሰራ እንደሆነ ገልጸዋል።

ከዚህም በተጨማሪ መስፍን ኢንጂነሪንግ በቦሌ ዞን በ35 ሺህ ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ይገነባል የተባለውን የኢንዱስትሪ ዞን ኮንትራት ወስዶ እየገነባ እንደሆነ ዜናው ጠቁሟል። መስፍን ኢንጂነሪንግ ከሶስቱ ቦይሊንግ ሀውሶች በተጨማሪ ለስኳር ፋብሪካዎቹ የሚያገለግሉ ላብራቶሪዎችን የመገንባት ኮንትራትም እንደወሰደ ኢቲቪ ጨምሮ ገልጿል። የኢትዮጵያ ህግ የፖለቲካ ፓርቲዎች በንግድ ውስጥ እንዳይሰማሩ ቢከለክልም፤ ባለቤትነቱ የሕወሀት የሆነው የትግራይ መልሶ ማቋቋም ኤንዳውመንት ፈንድ፤ በእንግሊዘኛው ምህጻረ ቃል ኤፈርት፤ ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ ጊዜ ጀምሮ በኢትዮጵያ በተለያዩ የንግድ ዘርፎች እንደተሰማራና ከሼክ አላሙዲን ቀጥሎ በአገሪቱ ውስጥ በብዙ ቢሊዮን ዶላር የሚቆጠር ቢዝነስ እንደሚያንቀሳቅስ ይታወቃል።(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## 16 የአውሮፓ ፓርላማ ምክር ቤት አባላት ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ከእስር እንዲፈታ ጥያቄ አቀረቡ

እንደፈረንጆች አቆጣጠር ዲሴምበር 18 ቀን 2012 ዓም ማለትም ከትናንት በስቲያ በዘረኛውና ጨካኙ የወያኔ አገዛዝ ያላግባብ ታስሮ እየተሰቃየ የሚገኘው የጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ጉዳይ እጂግ ያሳሰባቸው መሆኑን በመግለጽ 16 የአውሮፓ ፓርላማ ምክር ቤት አባላት ከእስር እንዲለቀቅ አስቸኩአይ ጥሪ አቅርበዋል። እነኝሁ የ አውሮፓ ፓርላማ ምክር ቤት አባላት ለይስሙላ በጠቅላይ ሚንስትርነት ለተቀመጠው ሃይለማሪያም ደሳለኝ በጻፉት ደብዳቤ እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር ከ2011 ጀምሮ በእስር ላይ የሚገኘው እስክንድር ነጋ ለረጂም ወራቶች ጠበቃ እንኩአን እንዳይጎበኘው የጭካኔ ርምጃ ተወስዶበት የነበረ ከመሆኑም በላይ የራሱም ሆነ የቤተሰቦቹ ንብረት በመንግስት ትእዛዝ እንዲወረስ መደረጉ አሳዛኝ እንደሆነባቸው ገልጸዋል።

የአውሮፓ ፓርላማ ምክር ቤት አባላቱ በደብዳቢያቸው እንደገለጹት የኢትዮጵያ መንግስት የሰው ልጆች ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ማክበር እንደሚገባው አሳስበው በአሁኑ ሰአት ኢትዮጵያን በጠቅላይ ሚንስትርነት እየመራት ያለው ሃይለማሪያም ደሳለኝ በኢትዮጵያ ተገቢ የሆነ ለውጥን የማምጣትና ሁኔታዎችን የመቀየር እንዲሁም ኢትዮጵያን አንድ ርምጃ ወደፊት የማራምድ እድል የተፈጠረለት መሆኑን ጠቅሰዋል። ቀጥለውም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እስክንድር ነጋ ከእስር ቤት የሚፈታበትን ሁኔታ ጠቅላይ ሚንስትሩ ማመቻቸት እንደሚገባው አሳስበዋል። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ሙስና እና ብልሹ አሰራርን በአደባባይ ያጋለጠው ሚኒስትር ዴኤታ ከኃላፊነቱ መነሳቱ ተዘገበ

ሰንደቅ እየተባለ የሚጠራው ጋዜጣ በዘገባው ላይ እንዳመለከተው ፤በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ተነስቶ ከነበረው ውዝግብ ጋር በተያያዘ ብልሹ አሰራር ሰፍኑአል በማለት ከሳምንታት በፊት በይፋ ያጋለጠው ሚኒስትር ዴኤታው ዳውድ መሐመድ ከኃላፊነቱ እንዲነሳ መደረጉ ታወቀ።

እንደ ሰንደቅ ዘገባ ሚኒስትር ዴኤታው ዳውድ መሐመድ ከኃላፊነቱ የተነሳበት ምክንያት ከባህልና ቱሪዝም ሚኒስትሩ አሚን አብዱልቃድር እና ከሌላዋ ሚኒስትር ዴኤታ ታደለች ዳለቾ ጋር የተፈጠረውን አለመግባባት ተከትሎ ነው። የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ምንጮችን ጠቅሶ ሰንደቅ እንደዘገበው አሻንጉሊቱ ደመቀ መኮንን በተገኙበት በተካሄደ ግምገማ ዳውድ ከሚኒስትር ዴኤታ ኃላፊነቱ እንዲነሳ ሆኗል። ዳውድ መሐመድ በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ውስጥ ሚኒስትር ዴኤታ በመሆን የባህል ዘርፍን ላለፉት ሁለት ዓመታት ሲመራ ቆይቱአል።

እንደ ሰንደቅ ዘገባ ዳውድ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በግልፅ የሚታየውን ሙስናና ብልሹ አሠራር በአደባባይ በመተቸቱ ከኃላፊነቱ መነሳቱ፣ ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለሚታገሉ ኃይሎች ሁሉ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ወያኔን ማስገደድ ወይም ማስወገድ የሞራልና ተፈጥሮዓዊ ግዴታ

ወያኔ/ኢህአዴግ የሰላማዊ በሮችን ሁሉ በመዝጋት በሀይል እየገፋና እየደፈጠጠ ስለ ሰላም የሚያወሩትን፣ ነጻነት የሚጠይቁትን፣ እንደወንጀለኛና ሽብርተኛ ታርጋ እየሰጠ ዴሞክራሲን ማፈኑ፣ ነጻነታችንን መግፈፉና የፖለቲካውን ምህዳር ማጥበቡ፤ የሀገራችን ህዝብ ሆ! ብሎ የተዘጋውን የሰላም በር ለማስከፈትና እንደ አረቡ አለም ጸደይ አቢዎት ተባብረን ስርአቱን የምናስወግድበት ቀን ሩቅ አይሆንም።

ሰሞኑንንም በኢትዮጵያ የሚገኙ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ይኼው የሰላሙ ትግል ተዳፍኖባቸው ለቀበሌና ለወረዳ ማሟያ በሚደረገው ምርጫ አንሳተፍም ብለዋል። ወያኔ ለዚህ ሁሉ ህዝብን ወደ አላስፈላጊ አማራጭ መግፋቱ አሁንም በታሪክ ተጠያቂ ያደርገዋል። በእኛ እምነት በሰላማዊ መንገድ የሚፈታ ማናቸውንም አማራጭ ሀሳቦችን ወደ ጠረንጴዛ በማምጣት መወያየት ስልጡን የሆነ፣ ስልጣን የህዝብና በህዝብ የሚመጣ መሆኑን ማረጋገጫ ስለመሆኑ አሁንም ደግመን ደጋግመን እንናገራለን።

ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ የኖብል የሰላም ሽልማት ሲቀበሉ ሰላማዊ የትግል አማራጭ ከወታደራዊ መፍትሄ እጅግ የተሻለ ስለመሆኑ የማያከራክር ቢሆንም በሰላማዊ መንገድ ብቻ ተጉዞ ሰላምን ማምጣት የማይቻልበት ሁኔታ መኖሩ፤ በዚህ ዓይነቱ ሁኔታ ውስጥ ደግሞ ኃይልን መጠቀም ግዴታ ብቻ ሳይሆን ከሞራል አንፃር ተገቢ ስለመሆኑ ያብራሩበት ነው። ከዚህም በተጨማሪ በአንዳንድ የዓለም ክፍሎችና ሁኔታዎች የኃይል አማራጭ ተገቢነት እየጨመረ መምጣቱን እና ለሰላም ሲባል ደም አፍሳሽ ጦርነት ውስጥ እንኳን ሊገባ እንደሚችል ማስረጃዎችን በመጥቀስ ያስገነዘቡበት ነው:: ወያኔ/ኢህአዴግ ደግሞ ለዚህ ትልቅ ምሳሌ ነው።

ባራክ ኦባማ ሲናገሩ *“ እውነቱን በመቀበል እንጀምር – ብጥብጥ ያለበት ቅራኔን በእኛ እድሜ ማስቀረት አንችልም። ለወደፊቱም ሕዝቦች – በግልም ሆነ በጋራ – ኃይልን መጠቀም አስፈላጊ ብቻ ሳይሆን ከሞራል አንፃርም ተገቢ የሚሆንበት ሁኔታ ይኖራል”*

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ሁለገብ ትግልን እንደ አማራጭ ሲያቀርብ የሰላማዊ ትግልን ውበት በመጠራጠር አልነበረም። ሰላምን መመኘት፣ ስለሰላም መዘመር፣ ስለሰላም ማስተማር፣ ስለሰላም መስበክ በእርግጥ ሰላምን ያስገኛል? ሰላም የሚደፈርሰው ሰዎች ስለሰላም ጥሩነት በቂ ግንዛቤ ስለሌላቸው ነውን? በጭራሽ! ሰላምን መመኘት፣ ስለሰላም መዘመር፣ ማስተማርና መስበክ ጥቅም ቢኖራቸውም ሰላምን ለማስገኘት በቂ አይደሉም፤ ሆነውም አያውቁም። ፕሬዝዳንት ኦባማ በዚሁ ንግግራቸው ያሉትም *ሲቪል ዜጎች በገዛ መንግሥታቸው የሚታረዱበት ሁኔታ፤ የእርስ በርስ ጦርነቶች ወይም አንድን የዓለም አካባቢ ሊያምሱ የሚችሉ ብጥብጦችና ሰቆቃዎችን ለመከላከል ኃይልን የመጠቀም አማራጭ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል።*

*ስለሆንም ወያኔ እየገፋን፣ በሀገራችን ዘረኝነትን እያነገሰብን፣ የዴሞክራሲን ጭራ እያጠፋብን፣ የነጻነት ብርሃንን እያጨለመብን ባለበት ሰአትም ሰላም ኃላፊነት መቀበል ነውና ስለ ሰላም መስዋዕትነትን እንከፍላለን።*

በሰላም ስም ባርነትን ማስፈን የአምባነገነኖች አንድ የጋራ ባህርይ ነው። አምባገነኖች ሰላም ማለት ሁሉም ሰው ከገዢዎች ተቆንጥሮ የሚሰጠውን መብት አመስግኖ ተቀብሎ፤ እንዲጫወት የታዘዘውን ባህርይ እየተጫወተ መኖር ማለት አድርገን እንድንወስድ ይፈልጋሉ። እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ሰላም፣ ነፃነትና ክብር የማይነጣጠሉ ነገሮች መሆናቸውን ነው። ስለ ሰላም ማሰብ የምንፈልገው ሙሉ ስብዕናችን በተረጋገጠበት ሁኔታ እንጂ ስብዕናችን በተዋረደበት ጊዜ ያለው አስፈሪ ዝምታ ማለት አይደለም።

ኦባማም እየተናገሩ ያሉት *“ሰላም የሚታይ ብጥብጥ አለመኖር ማለት አይደለም። ፍትሃዊ ሰላም ዘላቂነት የሚኖረው በእያንዳንዱ ግለሰብ ተፈጥሮዓዊ መብቶችና ክብር ላይ የተገነባ ሲሆን ነው።... ዜጎች የመናገር፣ የማምለክ፣ መሪዎቻቸውን የመምረጥ ወይም ያለፍርሃት የመሰብሰብ ነፃነታቸው በተገፈፉ ጊዜ ዘላቂ ሰላም አይኖርም።” ከዚህ ምን እንማራለን? መልሱ ለእኛው ለኢትዮጵያውያን ይሆናል..*

እኛ ኢትዮጵያውያንም እንደ ዜጋ የመናገር፣ መሪዎቻችንን የመምረጥና የመሰብሰብ፣ የእኩልነት መብት ማጣት ብቻ አይደለም የተፋጠጥነው። የዛሬ መብቶቻችንን ብቻ ሳይሆን የነገ ተስፋችንንም ሊያጨልምብን ከሚሞክር መሰሪ ሥርዓት ጋር ነው። በወያኔ አገዛዝ ዜጎች ተዋርደውና ተሸማቀው አሜን ብለው እንዲገዙ መደረጉ ብቻ ሳይሆን እንደ ሕዝብና እንደ አገር የመቀጠላችን ጉዳይ አጠራጣሪ እየሆነ በመምጣቱ ነፃነታችንና አንድነታችንን፣ ክብራችን የተጠበቀበት ሰላም ለማምጣት ወያኔን ማስገደድ ወይም ማስወገድ የሞራልና ተፈጥሮዓዊ ግዴታችን እና ኢትዮጵያዊ ማንነታችን ነው።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## የግንቦት 7 ሕዝባዊ ኃይል

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ህዝባዊ ሀይሉ "በሃገራችን በወያኔ አምባገነናዊ እብሪት ያልታፈነ፣ ያልተዋረደና ያልተዘረፈ የሃገሪቱ ዜጋ እንደማይገኝ ገልጾ፣ ሹማምንቱ በሃብት ላይ ሃብት፤ በድሎት ላይ ድሎት ሲጨምሩ፣ የአብዛኛው ኢትዮጵያዊ እጣ ፈንታ ግን መፈናቀል፣ መሰደድ፣ መንገላታት፣ መታሰር፣ መደብደብና መገደል ሆኗል" ብሎአል። "የወያኔ የአመጽ እብሪት በሕዝባዊ አመጽ የሚተነፍስበት ሁኔታ እስካልመጣ ድረስ፣ ወያኔ መብታቸውን ከመጠየቅ ውጭ ምንም እንከን የሌለባቸውን ንጹሃን ዜጎች ከማሰር፣ ሰቆቃ ከመፈጸም፣ ከመግደል ከማሳደድና ከማፈናቀል" እንደማይቦዝን ህዝባዊ ሐይሉ ገልጿል።

የግንቦት7 ህዝባዊ ሀይል " ዜጎች በሽብርተኛነት እየተከሰሱ በእድሜ ልክ እስራት ሲቀጡና ሰቆቃ ሲፈፀምባቸው የታዘባችሁ ወጣቶች፤ ለሃይማኖት እኩልነት በመታገላቸው በእስር ላይ እየማቀቁ፣ እየተገረፉና እየተሰቃዩ ያሉ የሙስሊም ምዕመናን ተወካዮች ጉዳይ የሚያሳስባችሁ ወገኖች፤ በቤተክህነትና በክርስትና ተቋማት ላይ እየተፈፀመ ያለው ደባ የሚያንገበግባችሁ ፤ ለወያኔዎችና ሽሪኮቻቸው እድገትና ምቾት ሲባል ከይዞታችሁ የተፈናቀላችሁ፤ ገቢን ሳይሆን ወገንተኛነትን መስፈረት ባደረገ መመዘኛ ከአቅም በላይ የሆነ የወያኔ ግብር፣ ታክስና መዋጮ የተማረራችሁ ነጋዴዎች፤ ማኅበራችሁ በወያኔ ፈርሶ ወይም ተጠልፎ የጋራ ድምፃችሁን የምታሰሙበት፣ ከቀጣሪያችሁ ከወያኔ ጋር ፍትሃዊ የጉልበታችሁን ዋጋ ክፍያ መደራደሪያ ያጣችሁ ላብአደሮች፣ መምህራን፣ የሲቪል ሰርቪስ ሠራተኞች፤ ምንም አይነት የአካዳሚ ነጻነት በሌለበት ሁኔታ ጥራቱን ያልጠበቀ ትምህርት እንድትከታተሉ የተፈረደባችሁ፣ ትምህርታችሁን ጨርሳችሁ ከየኮሌጁና ከየዩንቨርስቲው ስትመረቁ እጣችሁ ድንጋይ ማንጠፍ የሆነው ወጣት ተማሪዎች" ትግሉን ተቀላቀሉ ሲል ጥሪ አቅርቧል።

ህዝባዊ ሀይሉ "አደገኛ በረሃዎችንና ባህሮችን በማቋረጥ ለመሰደድ ልባችሁ እየከጀለ ላሉ ወጣቶች፣ በአረብ ሃገራት ለባርነት ስራ ተሸጠው እጣቸው ተገዶ መደፈር፣ በፈላው ወሃ መቀቀል፣ መደብደብ፣ መዋረድና ከፎቅ ላይ እየተወረሩ ክቡር ህይወትን ማጣት ለሆነው ሴቶች፣ ለሃገር አንድነትና ክብር መሰለፍ እንደ ወንጀል ተቆጥሮባቸው እንደ ባዕድ ጦር የተበተኑና የተገፉ በመከላከያ ሰራዊት ውስጥ በሚታየው ዘረኛነት እየተቃጠሉ፣ በሕዝብ ላይ ዝመቱ በተባሉ ቁጥር ከህሊናቸው ጋር መዳማት የመረራችው የኢትዮጵያ ወታደሮች እና በድህነት አስገዳጅነት፣ እንዲሁም በሌሎችም ማስፈራሪያዎችና ጫናዎች የወያኔ/ኢህአዴግ ድርጅቶች አባል የሆኑ ወገኖች በሙሉ" ጥሪውን ሰምተው ትግሉን እንዲቀላቀሉ ጠይቋል።

በhttp://www.ginbot7pf.org ድረገጽ ላይ የወጣው ዜና እንደሚያመለክተው ህዝባዊ ሀይሉ ራሱን በትጥቅና በሰው ሀይል አደራጅቷል።

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በሃይማኖት ላይ የሚያደርገውን

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በኩል የሚደረገው መሯሯጥ ተገቢ አለመሆኑን ገልጸው ይህ የቤተክርስቲያኒቱን አንድነት ከመጉዳት ሌላ ለማንም፣ ለወያኔም ጭምር የሚያስገኘው ጠቀሜታ የለም ብለዋል።

ከቤተክርስቲያን ሲወጡ ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው አንድ ምእመን በበኩላቸው ይሄ መንግስት ስጋዊ ፍላጎታችንን አሟልተን እንዳንኖር ፖለቲካዊ አፈናና ኢኮኖሚያዊ ጫና እያደረሰብን ኑሯችንን የቁም ገሃነም ሲያደርግብን የየትኛውም ሃገር ህዝብ ሊታገሰው በማይችል ትእግስት ታገስነው፤ አሁን ደግሞ እሱ አልበቃ ብሎት በመንፈሳዊ ሃብታችን በሃይማኖታችን መጣ አሁንም እንደለመድነው ዝም ካልነው ሰው ከሚያሰኙ ባህሪያት ምን ሊቀረን ነው? በማለት አንስተው እርሳቸው ከእንግዲህ የወያኔ መንግስት ለማስወገድ ለሚደረገው ትግል የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ለማድረግ ለራሳቸ ቃል መግባታቸውንና የኢትዮጵያ ህዝብም ይህንን ዘረኛና የከፋት ምንጭ የወያኔ ስርዓት ለማስወገድ እንዲነሳ ጥሪ አስተላልፈዋል።

የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች በሁለቱ ሲኖዶሶች መካከል ያለው ልዩነት በሰላም ተፈቶ የቤተክርስቲያኒቱ አንድነት እንዲጠበቅ ጸሎት እያደረጉ ባሉበት በዚህ ፈታኝ ወቅት ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ አገኛለሁ ብሎ ችግሩን ይበልጥ እንዲባባስ እያደረገ ባለው ዘረኛ፣ስግብግብና ጸረ-ሃይማኖት በሆነው የወያኔ መንግስት ላይ ቁጣቸው እየተባባሰ መምጣቱ ታውቋል።

(ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## መንግስት የለም ወይ ?
## መንግስት የለም ወይ ?

*(ህዝብ)*

ዘረኛው ህወሃት የኢትዮጵያ መንግስት እኔ ነኝ ይላል።ህዝቡ ግን መንግስት የለም ወይ እያለ መጠየቁን አላቆመም። ህወሃት የመንግስት ቅርፅና መልክ የሌለው ቡድን ስለሆነ ኢትዮጵያ ውስጥ መንግስት አለ ለማለት አይቻልም። ህወሃት መንግስት መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለማወቅ ብርቱ የሆነ የአቅም ችግር አለበት። ይሄን ደካማነቱን የተመለከተ ህዝብ ነው ድምጹን ከፍ አድርጎ መንግስት የለም ወይ ? መንግስት የለም ወይ? ብሎ የጠየቀው።ህወሃት የመንግስትነት ባህሪይ ቢኖረው ኑሮ ይሄን ድምጽ ማድመጥ በቻለ ነበር። እንዲህ ያለውን ድምጽ አሁን በዚህ ዘመን ያለ ይቅርና በዚያ በጨለማ ዘመን እግዚአብሄር ሾመን የሚሉ ነገስታት እንኳ ቢሆኑ ያደምጡት ነበር።ህወሃት ከጨለማው ዘመን ነግስታት እንኳ የማይሻል እጅግ ኋላ ቀር መሆኑን ከሚያሳዩን ድርጊቶቹ መካከል አንዱ ይሄው የህዝቡን ድምጽ መስማት አለመቻሉ ነው።

አንዳንድ ሰዎች ህወሃት የህዝቡን ድምፅ ለመስማት ፍላጎት እንዳይኖረው ያደረገው ምንድ ነው ብለው ይጠይቃሉ። መልሱ ተፈጥሮው ነው የሚል ነው። የህወሃት ተፈጥሮው የሚገለፀው በትእቢት እና በወንጀል ነው። ትዕቢቱና ሲፈፀመው የኖረው ወንጀሉ ደግሞ ከህዝብ ጋር አብሮ እንዳይኖር አድርገውታል። ህወሃት ራሱን ***"እኔ አውራ ነኝ ፤እኔ ከሌለው አገሪቷ ትፈርሳለች"*** እያለ በአደባባይ ሲፎክር መኖሩን እናውቃለን። ***"እኔ ከሌለው አገር ትፈርሳለች"*** የሚለው አባባል አንደኛ የትዕቢቱ ማሳያ ሁለተኛ ደግሞ ለአገሪቷም ሆነ ለህዝቧ ምንም ኃላፊነት እንደማይሰማው የሚያስረግጥ አባባል ነው። በአጠቃላይ ህወሃት ራሱን አለማወቁና ወሰን ያጣው ትዕቢቱ የህዝብን ድምፅ እንዳይሰማ አግደውታል። ከዚህ ትዕቢቱ መላቀቅ ባለመቻሉም የህዝብድ ድምጽ አድምጦ ከህዝብ ጋር የመኖርን ጥበብ ሊያገኞት አልቻለም።

***"እኛ አውራዎች ነኝ፤እኛ ከሌለን አገሪቷ ትፈርሳለች"*** የምትለዋ አባባል ያላዋቂዎች እንቶ ፈንቶ ብትሆንም እንዲህ እንላችኋለን፤

ህወሃቶች እውነት እውነት እንላችኋለን እናንተ ትሄዳላችሁ አገራችንም በሠላም ትኖራለች።የእናንተ አለመኖር አገራችንን አያፈርሳትም። እንዲያውም በተቃራኒው የእናንተ መኖር አገራችንን ከጎሬቤቶቿ ጋናንና ከኬኒያን ከመሳሰሉ አገራት በሁሉም ዘርፍ አንሳ እንድትታይ አደረጋት እንጂ የተሻለች አላደረጋትም።በእናንተ መኖር ምክንያት ዜጎች በተገኘው መንገድ ሁሉ መሰደድን መረጡ እንጂ ተረጋግተው በአገራቸው መኖርን አልመረጡም። ህወሃቶች አሁንም ስሙን እናንተ ባትኖሩ ኑሮ አገራችን ሠላሟ በዝቶ፤ ህዝቡ ተፋቅሮና ተከባብሮ፤ ብሄራዊ ስሜቱ በሚገባው ደረጃ ላይ ሁኖ፤ ሁሉም ኢትዮጵያ በአገሩ እኩል ከህግ በታች ሁኖ የሚኖርባት አገር በሆነች ነበር። ህወሃቶች አሁንም ስሙ የእናንተ መኖር አገሪቷን አፈርሳት እንጂ አልገነባትም።በእናንተ መኖር ምክንያት ህዝቡ "***በአገራችን ሠላም አጣን***" ብሎ እንዲማረር ሆነ እንጂ ደስ ብሎት እንዲኖር አልሆነም።

ህወሃቶች የዚያች አገር መንግስት ለመሆን የሞራልም ሆነ የእውቀት ብቃት እንደሌላቸው ባለፉት ሁለት አስርተ ዓመታት በአገራችን ላይ የፈፀሟቸው በደሎች ህያዋን ምስክሮች ናቸው። አዲስ አበባ ውስጥ መንግስት የለም ወይ ? መንግስት የለም ወይ ? የሚለው ጥያቄ የመጠየቁ መነሻም ትግሬን ነፃ አወጣለሁ ብሎ የተነሳው ይሄ ዘረኛ ቡድን ያችን አገር ለመምራት የሚያስችል ስነ-ባህሪይ ማሳየት ባለመቻሉ ነው።ይህ ቡድን ራሱን ከጋረደበት ጥላቻ አላቆ እንደ ሰው ልጅ አስቦ ከሰው ልጆች ጋር አብሮ ለመኖር የሚያስችለውን ባህሪይ በሙሉ መልሶ ላያገኘው አጥቶታል። ይሄ ቡድን የሠላምን ዋጋ አያውቃትም።ይሄ ቡድን ነፃነት ማለት ምን ማለት እንደሆነም ገና አልገባውም።ህወሃት ከሌሎች ጋር አብሮ መኖርንም አያውቅም። ከጎጠኛ አስተሳሰቡ ለመላቀቅም የአዕምሮ ብስለት የለውም። ይህ የጎጠኞች እና የትዕቢተኞች ስብሰብ የሆነው ማፊያ ቡድን ሳይፈለግ ከተቆናጠጠበት የስልጣን ኮርቻ ላይ መውረድ አለበት። ኢትዮጵያን እንዲህ ያሉ ዘረኞችና ወንበዴዎች ሊመሯት አይገባም።

ህወሃት የሚመራት ኢትዮጵያ ህዝቧ ቀንና ማታ የሚያለቅስባት፤ ልቅሶውን የሚያደምጥ መንግስት የሌለባት አገር ነች። ዛሬ በአዲስ አበባ ከተማ በሃና ማሪያም መንደር ነዋሪ የሆኑ ዜጎች ጥረውና ግረው የሡሩት ቤት ፈርሶ ህፃናት፤ እመጫቶች፤ በእድሜ የገፉ አዛውንት አባቶችና እናቶች ወደ ምትሄዱበት ሂዱ ተብለዋል።የት እንሄዳለን ብለው፤ የአገሪቷን ባንዲራ ይዘው የምንሄድበትን ቦታ ንገሩን ብለው ቢማፀኑም የያዙትን ባንዲራ ተነጥቀው ***"ከዚህ ሂዱ የኢትዮጵያ ህዝብ ድሮም የሚኖረው መንገድ ላይ ነው"*** ተብለው በህወሃት ቅጥረኛ ነፍሰ ገዳዮች አማካኝነት እንዲባረሩ ተደርጓል።

እናንተ ህወሃቶችና ከጎናቸው የቆማችሁ ሌሎች ሆይ ነውር ነገር ታውቁ እንደሆነ ያደረጋችሁት እና የተናገራችሁት ነውር ነው።እናንተ ግን ነውር ነገርን ታውቃላችሁ ለማለት በጣም እንቸገራለን። ለማንኛውም እንዲህ እንላችኋለን፤

የኢትዮጵያ ህዝብ ጎዳና ላይ መኖር የጀመረው ህወሃት አገሪቷን መቆጣጠር ከጀመረ ወዲህ ነው።ዛሬ በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች በአዲስ አበባ ጎዳናዎች ላይ እንዲኖሩ የሆነው ህወሃቶች የአገሪቷን ሃብት ዘርፈው ለራሳቸው ብቻ በማድረጋቸው ነው።ዛሬ በውጭ አገራት ባንኮች ከኢትዮጵያ ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ወጥቶ የተቀመጠው ብዙ ቢሊዮን ዶላር ዜጎች ጎዳና ላይ እንዲኖሩ ተደርጎ መሆኑን አበክረን ልናስታውሳችሁ እንወዳለን።ይሄ ዝሪፊያችሁ ነው የኢትዮጵያ ህዝብን ጎዳና ተዳዳሪ እንዲሆን ያደረገው እንጂ ሌላ አይደለም።

እናንተ ጎጠኛ ህወሃቶች ስሙ!!!

ዛሬ እናንተ ልጆቻችሁን በአሜሪካና በአውሮፓ እንዲሁም በቻይና ልካችሁ የምታስተምሩት ከድሃው ኢትዮጵያዊ ዘርፋችሁ መሆኑን እኛ እንድንነግራችሁ ትፈልጋላችሁን? የእናንተ ልጆች ተንደላቀው ሲማሩ ሌላው ኢትዮጵያዊ ግን ጎዳና ተዳዳሪ ሁኖ በድንቁርና ውስጥ እንዲኖር የፈረዳችሁበት መሆኑንስ አትገነዘቡምን? የዘመኑ ባለስልጣናት ለራሳችሁ ባለ ብዙ ፎቅ ቤቶችን ሠርታችሁ ተንደላቃችሁ ስትኖሩ ከራሳችሁ የተረፈውንም በብዙ ሺህ ብር እያከራያችሁ ደስ ብሏችሁ ስትኖሩ ድሆች በላባቸው ጥረውና ግረው የሰሩትን ቤቶች አፍርሳችሁ ሜዳ ላይ መጣላችሁን ህዝቡ የማያይ ይመስላችኋልን ?እኛም ሆንን ሌሎች ሁሉንም እያየን እና እየሰማን ነው።ከህዝብ ተሰውሮ የሚቀር አንዳችም ነገር የለም።

እናንተ ***"እኔ"*** ብቻ ማለትን የምታውቁ ህወሃቶች ስሙ !!!

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ እንዲህ እንደ እናንተ ዘመን ጎዳና ላይ የሚኖር ዜጋ ታይቶ አይታወቅም። እንዲህ አይነት ሁኔታ በጎሬቤት አገሮችም አልታየም። በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች በአገሪቷ ዋና ከተማ ጎዳና ላይ የሚኖሩት እናንተ እንመራታለን በምትሏት ኢትዮጵያ ብቻ ነው። ጭካኔያችሁ ወደር የሌለው በመሆኑና አገራዊ ስሜት በማጣታችሁ የአዲስ አበባ ጎዳናዎች በሺዎች በሚቆጠሩ ጎዳና ተዳዳሪዎች ሊሞሉ ችለዋል ።

***"ኢትዮጵያን የምንሰበር እኛ፤ የምንጠግንም እኛ"*** ብላችሁ በቅዥት የምትኖሩ ህወሃቶች አሁንም ስሙ!!!
መተማመኛችሁ ጠመንጃችሁ መሆኑን እናውቃለን።እናንተ ከጠመንጃ ወዲያ ማሰቢያ አካል እንደሌላችሁም ደህና አድርገን እንገነዘባለን።እኛ ግን እንዲህ እንላችኋለን ያ ስትግድሉት አልቅሶ ዝም ያላችሁ ህዝብ ሞትን የሚንቅበት ግዜ እሩቅ አይሆንም።ካሁን ወዲያ ምን ሊመጣ የሚልበት ግዜም እየመጣ ነው።ለዲኑ፤ለሃይማኖቱ፤ለነፃነቱ መሞት ክብርና ጀግንነት መሆኑን አምኖ የሚቀበልበት ግዜ ደርሷል።ያን ግዜ ያ የተሞረኮዛችሁት ጠመንጃ የሸንበቆ ምርኩዝ ሆኖ ተሰብሮ የሚወጋችሁ መሆኑን ልናሳውቃችሁ እንወዳለን።ያ ከመሆኑ በፊት ግን ከህዝብ ጎራ እንድትቀላቀሉ ሳንመክራችሁ አናልፍም።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!**

---

## አራት ኢትዮጵያዊያን ጋዜጠኞች በነጻነት የሔልማን

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

መቆየቱ የሚታወስ ሲሆን፣ ይህን ሽልማት ለነኝህ ታዋቂ ጋዜጠኞች የሸለመው ተቋም ጋዜጠኞቹ ሽብርተኛ ሳይሆኑ በኢትዮጵያ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብጥ አፈኛኝ ጠቁመውኛ ጠጋፍተው የሚጭሉጥኝ ሑሉ ያደረጉ ኛጨው ብሷጨዋል።

ሄልማን ሃሜትስ በሁለት ታዋቂ አሜሪካዊያን ጋዜተኞች ስም የተሰየመ ተቋም ሲሆን በሂዩማን ራይትስ ዋች ስር የምኒተዳደርና በየዓመቱም በየሃገሮቻቸው ሃሳብን በነጻነት በመግለጽ ትግል ታዋቂ የሆኑ ጋዜጠኞችን በመምረጥ የሚሸልምና የሚያበረታታ ተቋም ነው።

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በሃይማኖት ላይ የሚያደርገውን

. . . (ከገጽ 2 የዞረ)

የወያኔ አገዛዝ ወኪል ፓትርያርክ ለማስቀመጥ ይረዱኛል ብሎ ካስመረጣቸው የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት መካከል ሶስት አራተኛው የአንድ ብሄረሰብ አባላት መሆናቸው የታወቀ ሲሆን ቀሪዎቹ ደግሞ ለቀድሞው ፓትሪያርክ አቡነ ጳውሎስ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ከቤተ ክህነት ወጪ እንዲሆን አድርገው ሃመር መኪና የመሸለምን ቀዳሚ ተግባር ሲያከናውኑ የነበሩ ህሊናቸውን የሸጡ ግለሰቦች መሆናቸውን ዘጋቢያችን ገልጿል።

.....................................................................................................................................

## በዘረኛው የወያኒ አገዛዝ ቁጥጥር ስር የወደቀው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሰራተኞችን ማባረሩን ቀጥሉኣል

ደረጃ በደረጃና ኢትዮጵያዊያን ምን አየተከናወነ እንዳለ እንኩዋን በማያስተዉሉበት መንገድ በዘረኛው የወያኒ ኣገዛዝ ቁጥጥር ስር የወደቀው የኢትዮጵያ ኣየር መንገድ ዘርን መሰረት ያደረገ ኣድሉኣዊ ኣሰራርን ከማስፈን ባለፈ የሊየሎች ብሂረሰብ ተወላጆችን ከቁልፍ ቦታዎች በማስወገድና በትግራይ ተወላጆች በመተካቱ የሚታወቅ ሲሆን ይህ ኣሰራር ኣሁንም ባለበት ሁኒታ እንደቀጠለና ወደ ሊየሎች ሰራተኞችም አየተዛመተ አንደሚገኝ፣ ለዝግጂት ክፍላችን በኢ ሚእይል የደረሰ ጥቆማ ኣጋለጠ።

ለደህንነታቸው ሲባል ስማቸው አንዳይገለጥ የፈለጉ ኣንድ የድርጂቱ ሰራተኛ ይህን መልክቲን ለኢትዮጵያዊያን ኣስተላልፉልኝ በማለት የላኩት ኢ ሚአይል አንደሚያመለክተው በዘረኛው የወያኒ ኣገዛዝ ባለስልጣናት የተወረረው የኢትዮጵያ ኣየር መንገድ ማንም ሰሚ በሊየለበት ሁኒታ በጥቂት የኣንድ ብሂአረሰብ ኣባላት የበላይነት እየተመራና፣ ከዚህ ብሂረሰብ ውጭ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን ደግሞ ከተለያዩ ኣድሎዎች አስከ ከስራ መባረር የሚያደርስ ግፍና በደል አየተፈጸመባቸው ነው ብለዋል።

እኚሁ የኢትዮጵያ ኣየር መንገድ የቀድሞ ሰራተኛ አንደሊየሎች ጉዋደኞቻቸው የዘረኛው ወያኒ አገዛዝ ሰለባ መሆናቸውንና ከስራም መባረራቸውን ለዝግጂት ክፍላችን በላኩት ኢ ሚእይል ገልጸዋል። በመጨረኃም በላኩት ኢ ሚይል ላይ እንደገለጹት የኢትዮጵያ ኣየር መንገድ በሰራተኞቹ ላይ አያደረሰ ያለውን በደል ለመቀነስም ሆነ ድርጂቱ ያለበትን ኣደጋ ለመቀነስ በውጭ ሃገር የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ጉልህ ኣስተዋጾ ሊኖራቸው አንደሚችል ያላቸውን የስራ ልምድ ዋቢ በማድረግ ገልጸዋል። በመሆኑም በውጪ ሃገር የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን የኢትዮጵያ ኣየር መንገድን መጠቀም ቢያቁኣርጡ፣ ኣየር መንገዱ ኣጣብቂኝ ውስጥ ሊገባ አንደሚችልና ምናልባትም በሰራተኞቹ ላይ የሚፈጽመውን ግፍ ሊቀንስ አንደሚችል ኣስተያየታቸውን ሰጥተዋል። የኢትዮጵያ ኣየር መንገድ ኣብዛኛው ገቢው በውጪ ሃገር ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን የሚያገኘው ገቢ አንደሆነም ኣክለው ገልጸዋል።

የግንቦት ሰባት ንቅናቂ ሪዲዩ በኢትዮጵያ ኣየር መንገድ ውስጥ አየተፈጸመ ያለውን በደልና ግፍ አየተከታተለ ሲዘግብ መቆየቱ ኣይዘነጋም።

## የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በኢህአዴግ ፕሮፓጋንዳ መማረራቸው ተዘገበ

ዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ከሞተ ወዲህ በየመድረኩና በመንግስት መገናኛ ብዙሃን “የመለስን ራዕይ እናሳካለን” በሚል የሚነገረው ፕሮፖጋንዳ እጅግ የበዛና አሰልቺ እንደሆነባቸው በስልክ ያነጋገራቸውን አንዳንድ የአ/አ ከተማ ነዋሪዎች ዋቢ በማድረግ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቲእሊእቪዥን ኢሳት ዘገበ።

እንደ ኢሳት ዘገባ እንደኢትዮጵያ ቴሌቪዥን እና ራዲዮ ያሉ የመንግስት መገናኛ ብዙሃን ወሬያቸው ሁሉ ከመለስ ራዕይ ማሳካት ጋር የተያያዘ ከመሆኑም ባሻገር አቀራረቡም ሆነ የድግግሞሹ ብዛት አድማጭና ተመልካቹን የሚያሰለች መሆኑን የከተማ ነዋሪዎቹ ተናግረዋል።

የትኛውም ዓይነት ስብሰባዎችን ለመለስ ጸሎት በማድረግ መጀመር የግድ እየሆነ መምጣቱን ለኢሳት የጠቀሱት አስተያየት ሰጪ  በአዲስ አበባ አስተዳደር በአንዳንድ መ/ቤቶች ደብዳቤ መጻጻፊያ ማሳረጊያ ላይ “ከሰላምታ ጋር” በሚለው የመልካም ምኞት መግለጫ ምትክ “የመለስ ራዕይ ይሳካል!” በሚል መጻፍ መጀመሩ ነገሩ የቱን ያህል ግለሰብ ወደ ማምለክ ደረጃ መውረዱን የሚያሳይ ተጨባጭ ምሳሌ ነው ካሉ በሁኣላ  መለስን ማምለክ መቼ እንደሚያቆምም አሳሳቢ እየሆነ መምጣቱን ጠቁመዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ በየጎዳናውና በመንግስት መ/ቤቶች ዘረኛውና አምባገነኑ መለስን የሚያሞግሱ መፈክሮች  የመስቀሉ ሥራም ተጠናክሮ መቀጠሉን የጠቆሙት ሌላው የአ/አ ነዋሪ አስተያየት ሰጪ በህይወት የሚገኙት ከፍተኛ አመራር አካላት ተብየዎች ቀጣዩን የአገሪቱን ዕጣ ፈንታ በሞተ ሰው ራዕይ ለማስቀጠል ሌት ተቀን በሚደረገው ውትወታ ለምን የሙጢኝ እንዳሉ ግልጽ አይደለም ብለዋል ሲል ኢሳት ገልጹአል።

## 16 የአውሮፓ ፓርላማ ምክር ቤት አባላት ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ፍሪደም ናው (ነጻነት አሁኑኑ) የተሰኘው ተቁአም ዳይሬክተር ማራን ቱርነር በአለማችን የሰው ልጆች ሃሳባቸውን በነጻነት የመግለጽ መብት ዓለማቀፋዊ መብት እንደሆነና ይህም በኢትዮጵያ መንግስት ዘንድም ሊከበር እንደሚገባው ገልጸው፣ ጋዜጠኛ እስክንድርም የታሰረው ሃሳቡን በነጻነት በመግለጹ ብቻ እንደሆነ ታውቆ ከእስር ባስቸኩአይ ሊለቀቅ እንደሚገባው በአጽንኦት አሳሰበዋል።

ፍሪደም ናው (ነጻነት አሁኑኑ) የተሰኘው ተቁአም ዳይሬክተር ማራን ቱርነር በአለማችን የሰው ልጆች ሃሳባቸውን በነጻነት የመግለጽ መብት ዓለማቀፋዊ መብት እንደሆነና ይህም በኢትዮጵያ መንግስት ዘንድም ሊከበር እንደሚገባው ገልጸው፣ ጋዜጠኛ እስክንድርም የታሰረው ሃሳቡን በነጻነት በመግለጹ ብቻ እንደሆነ ታውቆ ከእስር ባስቸኩአይ ሊለቀቅ እንደሚገባው በአጽንኦት አሳሰበዋል።

ይህ የአውሮፓ ፓርላማ ምክር ቤት አባላት ለሃይለማሪያም ደሳለኝ የጻፉት ደብዳቤ ፍሪደም ናው (ነጻነት አሁኑኑ) በተሰኘው ድርጂት ድረ ገጽ ላይ የሚገኝ ሲሆን በዚሁ ደብዳቤ ላይ ሚስስ አና ጎሜዝን ጨምሮ በርካታ ታዋቂ የ አውሮፓ ፓርላማ ምክር ቤት አባላቶች በፊርማቸው አረጋግጠዋል።

ይህ በንዲህ እንዳለ የወያኔው የይስሙላ ፍርድ ቤት ችሎት በእነ አንዱለም አራጌ የክስ መዝግብ በሥር ፍርድ ቤት በሽብር ወንጀል ጥፋተኝነት የተፈረደባቸውን የፖለቲካ ፓርቲ አመራር አባላትና ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ይግባኝ ክርክር ማድመጡን ከአዲስ አበባ ዘጋቢያችን በላከልን ሪፖርት ገልጹአል።

እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ያለ ጠበቃ በራሱ ክርክር የቀረበ መሆኑ የታወቀ ሲሆን፣ "ዐቃቤ ህግ ያለምንም ማስረጃ፣ ሠነድ፣ የስልክ ጠለፋ እና የሰው ምስክር እኔን የግንቦት 7 አባል ያደረገኝ ፍጹም ሀሰት ነው፣ እንዲህ ብሎ ለመፈረጅም የተጠቀመበት በሚዲያ ያወጣሁትን ይፋዊ ጽሑፍ እንደማስረጃ በመጠቀም፣ በማቋቋም ላይ የነበረውን የሲቪክ ተቋም በማየት እና በአንድነት ፓርቲ ያደረኩትን ህዝባዊ ንግግር በመጠቀም ብቻ ነው" በማለት መናገሩ ታውቁአል።

ጋዜጠኛ እና የፖለቲካ አክቲቪስት የሆነው እስክንድር ነጋ ለፍርድ ቤቱ ሲናገር "ዐቃቤ ህግ እኔን እና ግንቦት ሰባትን በዓላማ አገናኝቶናል፤ ነገር ግን የእኔ እና የግንቦት ሰባት ዓላማ አይገናኝም፤ እኔን የግንቦት ሰባት አባል ስለመሆኔ፣ የግንቦት ሰባት ጋዜጣ ያወጣውን ዜና ዋቢ በማድረግ ነው የፈረጀኝ፣ ከፍተኛው ፍርድ ቤትም የፈረደው" በማለት አክሎ ገልጹአል። በማያያዝም "በሀገሬ ላይ ያለው ምርጫ ህገመንግስቱ እንደሚለው ህጋዊና ፍትሃዊ ስላልሆነ ህገመንግስቱ የሚለው እንዲተገበር የዜግነት ግዴታ አለብኝ። ለዚህም በህጋዊ መንገድ ታግያለሁ፤ ምንም ዓይነት ነገር ዐቃቢ ህግ እንደሚለው በእቡዕ የሆነ ነገር የለም፣ በአደባባይ የተናገርኩት፣ በሚዲያ የጻፍኩት፣ የገለጽኩትና የተናገርኩት ነው አንድ እንኳ በእቡዕ የቀረበ ነገር የለም" በማለት በዝርዝር ማስረዳቱን ዘጋቢያችን ገልጹአል። በመጨረሻም እስክንድር  " ክቡር ፍርድ ቤት ፤ አበበ በለው ጥፋተኛ የተባለው ከኔ ጋር ስለተገናኘ ነው ። ከኔ ከመገናኘቱ በፊት እንዲህ አልተባለም፤ እኔ ግንቦት ሰባት በመባሌ ነው  እርሱም ግንቦት ሰባት የተባለው፤ ከክሱ በፊት ከእርሱ ጋር ያደረኩትን ቃለመጠይቅ ነው በኋላ ለተፈጠረው ክስ እንደማስረጃ ያቀረቡብኝ፣ እንደ እኔ በግፍ ግንቦት ሰባት የተባሉ በውጪ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ብዙ ናቸው " ማለቱ ታውቁአል።

## ሙስና እና ብልሹ አሰራርን በአደባባይ ያጋለጠው

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

አስደንጋጭ መልዕክት ያስተላለፈ ነው ሲሉ አንድ የመ/ቤቱ ባልደረባ አስተያየታቸውን መስጠታቸውን ገልጻጹአል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በተለያዩ ክልሎች በሚገኙ ተቁአማት ውስጥ ቁልፍ በሆኑ ቦታዎች የራሱን ግለሰቦች፣ ቁልፍ ያልሆኑና ብዙም አስቸጋሪ ባልሆኑ ቦታዎች ደግሞ ለሆዳቸው ባደሩና እንደፈለገው የሚያሽከረክራቸው የሃገር ከሃዲዎች በመሾም፣ እነኝህ ሹመኞች ለማፍነገጥ ሲሞክሩ ከስልጣን ማባረርን እንደመሳሪያ ሲጠቀምበት መቆየቱ በስፋት መዘገቡ ይታወሳል።

## መስፍን ኢንጂነሪንግ ኩባንያ የ2.6 ቢሊዮን

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ኤፈርት ከተቋቋመ ጊዜ ጀምሮ ከመንግስት በሚያገኘው ፖለቲካዊና ወለድ-የለሽ የብድር አገልግሎት በመታገዝ የመንግስት የግንባታ ፕሮግራሞችን ያለተቀናቃኝ በመወሰድ የሌሎች የግል ባለሀብቶችን ስራ እንደሚያቀጭጭ አስተያየት ሰጪዎች ይናራሉ። ስለትግራይ መልሶ ማቋቀም ኤንዳወውመነንት ፈንድ የተጠየቁ የህወሀት አመራሮች ገንዘቡን በትግሉ ሰዓት ያፈራነው ነው ባለቤትነቱም የትግራይ ህዝብ ነው ሲሉ መልስ የሚሰጡ ሲሆን፤ ድርጅቱ ከተቋቋመ እስካሁን ድረስ ምንም አይነት የውጭ ኦዲት እንፈደማያውቀው የራሱ ህሀወት ባለስልጣናት ይተቻሉ። ኤፈርት ከመጀመሪያው የድርጅቱ ቦርድ ሊቀመንበር አቶ ስዬ አብርሀ ጊዜ ጀምሮ ከንግድ ባንክ ዋስትና የለሽ የብድር አገልግሎት ያገኝ እንደነበር የሚነገር ሲሆን፤ ከወራት በፊት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተበላሹ ብድሮች በሚል የኤፈርትን እዳዎች መሰረዙን መዘገባችን ይታወሳል። በአሁኑ ሰዓት የኤፈርት የቦርድ ሊቀመንበር የሟቹ ጠቅላይ ሚኒስትር ባለቤት ወ/ሮ አዜብ መስፍን ናቸው።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ  የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB  በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና  በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ  5980 KHz እና  በ 60 MB  4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።  g7radio@ginbot7.org